## የኤጀንሲ ስም፥

የእስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት

## የተልዕኮ መግለጫ፥

የእስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት (OSSE - ኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ.) ተልዕኮ የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች ጥሩ ትምህርት እንዲያገኙ እና በኮሌጅ ውስጥ፣ በስራ ዓለም እና በህይወት ውስጥ ስኬታማ እንዲሆኑ ለማዘጋጀት እንቅፋቶችን ማስወገድ እና ጥርጊያ መንገድ መፍጠር ነው።

## የኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ. ስራ ምንድን ነው?

የእስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት (OSSE - ኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ.) ለዲሲ ነዋሪዎች የትምህርት ጥራትን የማሳደግ ኃላፊነት ያለበት የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የትምህርት ኤጀንሲ ነው። ኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ. ለአሜሩካ የትምህርት መምሪያ የዲስትሪክቱ ግንኙነት ሆኖ የሚያገለግል ሲሆን የሚከተሉትን ቁልፍ ተግባራቶቹን ለማሳካት ከዲስትሪክቱ ባህላዊ እና የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ጋር በቅርበት ይሰራል፥

- በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ የሚተዳደሩ ሁሉንም የፌደራል የትምህርት ፕሮግራሞች እና ተዛማጅ የገንዘብ ድጎማዎችን መቆጣጠር።
- ከትምህርት ቤት፣ ከኮሌጅ፣ እና በሥራ ዓለም ከሚጠበቁ ዝግጁነቶች ጋር አብረው የሚሄዱ በእስቴት አንጻር ያሉ ደረጃዎችን ማጎልበት።
- ብቁ የሆኑ በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች ከፍተኛ ጥራት ያለው የልጅ እንክብካቤ እና አጠቃላይ ቅድመ መዋዕለ ሕጻናት ማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ።
- የዲስትሪክቱ በጣም ተጋላጭ የሆኑ ተማሪዎችን ለማገዝ ግብዓቶችን እና ድጋፎችን መስጠት።
- አመታዊውን ለኮሌጅ እና ለስራ ዓለም ዝግጁነት የምዘና አጋርነት (PARCC - ፒ.ኤ.አር.ሲ.ሲ)፣ እና ዲሲ ሳይንስ፣ የእስቴት አቀፍ የተማሪዎች የትምህርት ብቃት ፈተናዎችን ማስተዳደር።
- የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ የዲስትሪክቱ ተማሪዎች ከቤት - እስከ - ትምህርት ቤት፣ ክልላዊ የትምህርት መጓጓዣ አገልግሎት መስጠት።
- ብቁ ለሆኑ የዲስትሪክቱ ተማሪዎች በዲሲ ውስጥ እና በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ የሕዝብ እና የግል ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት የገንዘብ ድጋፍ ማመቻቸት።
- የጤና እና የሰውነት ማጎልመሻ ግንዛቤን መጨመር እንዲሁም ዓመቱን ሙሉ የነጻ ምግብ ተደራሽነት መኖሩን ማረጋገጥ።
- የሁሉንም ተማሪ-አትሌቶች የትምህርት ልምዶች የሚያዳብረውን በትምህርት ቤቶች መካከል የሚካሄደውን የአትሌቲክስ ውድድርን የሚያዘጋጀውን የዲሲ እስቴት አትሌቲክስ ማህበርን (DCSAA - ዲሲ.ኤስ.ኤ.ኤ) መቆጣጠር።
- ስለ በባህላዊ እና ህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤቶች እና የተማሪ ውጤቶች እስቴት አቀፍ የትምህርት ቤቶች ዳታ ማቅረብ።
- እያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ ይሆናል በሚለው ድንጋጌ መሠረት ለትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ የሚውሉ አዳዲስ እቅዶች የመንደፍ እና የመተግበር ተግባራትን መምራት።

## የተመረጡ አገልግሎቶች፥

የዲሲ የትምህርት ክፍያ እገዛ የገንዘብ ድጋፍ (DCTAG - ዲሲ.ቲ.ኤ.ጂ) እና የሜየር የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት እድል ፕሮግራም

የዲሲ የትምህርት ክፍያ እገዛ የገንዘብ ድጋፍ (DCTAG - ዲሲ.ቲ.ኤ.ጂ) በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ላሉ ኮሌጅ ለመግባት ለሚፈልጉ ነዋሪዎች የከፍተኛ የትምህርት አማራጮችን ለማስፋፋት በ 1999 በኮንግረንስ የተፈጠረ ነው። ሁሉም የህዝብ ተቋማት፣ በታሪክ የጥቁር ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች (HBCUs)፣ እና በዋሽንግተን የከተማ ክልል ውስጥ ያሉ ለትርፍ ያልሆኑ የግል ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች በዲሲ.ቲ.ኤ.ጂ ውስጥ ለመሳተፍ ብቁ ናቸው።

ዲሲ.ቲ.ኤ.ጂ በአመሪካ፣ በጉዋም እና በፖርቶ ሪኮ በመላው ባሉ የህዝብ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በእስቴት ውስጥ እና ከእስቴት ውጭ መካከል መካከል ያሉ እስከ $10,000 የሚደርስ የትምህርት ክፍያ ልዩነቶችን በመደጎም ለዲስትሪክቱ ነዋሪዎች የከፍተኛ ትምህርት ምርጫዎች ያሰፋል። በተጨማሪም ዲሲ.ቲ.ኤ.ጂ በዋሽንግተን ዲሲ፣ በዲሲ የከተማ ክልል፣ የማህበረሰብ ኮሌጆች የሚገኙ የግል ኮሌጆች እና በመላው ሃገሪቱ ለሚገኙ የግል በታሪክ የጥቁር ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች (HBCUs) በዓመት እስከ $2,500 የአሜሪካ ዶላር የትምህርት ክፍያዎችን ይሰጣል። ዲሲ.ቲ.ኤ.ጂ በአሁኑ ወቅት ከ 300 በላይ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች አሉት። ኮሌጅዎ ወይም ዩኒቨርሲቲዎች ዲሲ.ቲ.ኤ.ጂ ውስጥ ይሳተፍ ወይም አይሳተፍ እንደሆነ ለማወቅ እባክዎትን በሚከተለው ድህረ ገጽ ላይ የተሳታፊ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ዝርዝራችንን ይጎብኙ፥ https://osse.dc.gov/dctag

የሜየር የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት እድል ፕሮግራም በተመረጡ ቦታዎች ባሉ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በአስፈላጊነት ላይ የተመሰረተ የትምህርት ድጋፍ ብቁ ለሆኑ የተባባሪ ዲግሪ ወይም የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ለሚከታተሉ የዲሲ ነዋሪዎች ይሰጣል። ፕሮግራሙ በተማሪው የገንዘብ ድጋፍ እና ትምህርቱን ለመከታተል በሚያስፈልጉት ወጪዎች መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት የተነደፈ 'የመጨረሻ-ዶላር' ሽልማት ነው። በተለምዶ፣ የሜየር ስኮላርሺፕ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት ዘመን ላይ እስከ $4,000 የአሜሪካ ዶላር፣ ለተባባሪ ዲግሪ እስከ አራት ዓመት ድረስ፣ እና ለመጀመሪያ ዲግሪ ደግሞ እስከ ስድስት ዓመት ድረስ ያገኛሉ። የገንዘብ ድጋፉ ቀድሞ ለመጣ - ቀድሞ መስጠት በሚለው መርህ የሚሰጥ ሲሆን አመልካቾች በየዓመቱ ደግመው ማመልከት አለባቸው።

የሜየር የመጀመሪያ ዲግሪ የትምህርት እድል ፕሮግራም በዲሲ የከተማ ክልል ውስጥ በተመረጡ ኮሌጆች እና ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን ለሚከታተሉ የዲስትሪክቱ ነዋሪዎች ድጋፍ ይሰጣል። የትምህርት ድጋፉ ተቀባዮች ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አቻ የምስክር ወረቀት (ለምሳሌ፥ GED) ያገኙ መሆን አለባቸው። ለተጨማሪ መረጃ እና ለማመልከት እባክዎትን የሜየር ስኮላርሺፕ ድህረ ገጽን ይጎብኙ፥ https://osse.dc.gov/mayorsscholars

## የተማሪዎች መጓጓዣ (OSSE DOT - ኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ ዲ.ኦ.ቲ)

የተማሪ መጓጓዣ ክፍል (OSSE DOT- ኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ ዲ.ኦ.ቲ) በዲስትሪክቱ ውስጥ የሚገኙ ብቁ የሆኑ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎችን በየቀኑ፣ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ እና በሰዓቱ የሚያጓጉዝ ክልላዊ የትራንስፖርት ስርዓት ነው። ኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ ዲ.ኦ.ቲ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ከሚገኙ አራት አውቶቡስ ማቆሚያዎች በመነሳት በየቀኑ በግምት እስከ 34,000 ማይሎች የሚጓዙ ከ 521 በላይ አውቶቡሶች አሉት።

የወላጅ የመረጃ ማዕከል (ስልክ ቁጥር፥ (202) 576-5000) የተማሪን የመጓጓዣ ጉዳይ በፍጥነት ተደራሽ በማድረግ ጥራት ያለው የደንበኛ አገልግሎት ለመስጠት በትጋት ይሰራል። የደንበኛ አገልግሎት ተወካዮች እስከ 20 ደቂቃዎች ወይም ከዛ በላይ የሚሆኑ የአውቶቡስ መዘግየቶችን በተመለከተ እና በአስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ወይም በሌሎች ድንገተኛ ሁኔታዎች ምክንያት የጉዞ መስመር እና መርሃግብር ለውጦችን ለተማሪዎች ወላጆች እና ለአሳዳጊዎች ለማሳወቅ ስልክ የሚደውሉ ይሆናል። ጥያቄዎች ለወላጅ የመረጃ ማዕከል በሚቀርቡበት ጊዜ የደንበኞች አገልግሎት ተወካዮች ተማሪው በዛ ቅጽበት ያለበትን ሁኔታ ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት፣ ለወላጅ ስጋት መፍትሔ ለማግኘት እና ተገቢ የሆኑት የወላጆችን ጥያቄዎች ለመመለስ የጂፒኤስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም፣ ከጣቢያዎች እና ከሾፌሮች ጋር ይነጋገራሉ እንዲሁም በተማሪው መረጃ ላይ ጥናት ያደርጋሉ።

## ለህጻን እንክብካቤ ለመክፈል እርዳታ፥ የህጻን እንክብካቤ ቫውቸር ፕሮግራም

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች ለልጆች እንክብካቤ አገልግሎቶች መክፈል እንዲችሉ የሚያግዝ በፌደራል መንግስት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት የልጆች እንክብካቤ እርዳታ ፕሮግራምን ያካሂዳል። የልጆች እንክብካቤ ቫውቸር ፕሮግራም ለቤተሰቦች የተለያዩ የሕጻናት እንክብካቤ አማራጮችን ይሰጣል። እነዚህ የተለያዩ መርሐ-ግብሮች እና ፕሮግራሞች መኖራቸው ቤተሰቦች ፍላጎታቸውን በተሻለ ሁኔታ የሚያሟላውን አማራጭ እንዲመርጡ ያስችላቸዋል።

ቤተሰቦችዎ የሰው ሃይል አገልግሎት መምሪያ፣ የኢኮኖሚ ደህንነት አስተዳደር [የልጆች እንክብካቤ አገልግሎት ክፍል ]ጽ/ቤትን በስራ ሰዓት በመጎብኘት ለሕጻናት እንክብካቤ ቫውቸር ማመልከት ይችላሉ። በተጨማሪም እርስዎ በመረጡት ፍቃድ የተሰጠው ደረጃ II የልጆች እንክብካቤ አገልግሎት አቅራቢ በቀጥታ ማመልከት ይችላሉ (ተቋሙ ለመቀበል ፈቃድ ያለው መሆን አለበት)።

ድጋፍ የተደረገለት የሕፃናት እንክብካቤ አገልግሎት ማመልከቻ ካጠናቀቁ እና ካስገቡ በኋላ በመጀመሪያ የመቀበያ ጣቢያዎት ከብቁነት ሰራተኛ ጋር የቃለ መጠይቅ መርሃ ግብር ማዘጋጀት አለብዎት። በቃለ መጠይቁ ወቅት የብቁነት ሰራተኛው ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ሁሉንም ተገቢ የብቁነት መመዘኛዎች በደንብ ይገነዘባል። ፕሮግራሙ ብቁ ለሆኑ ህፃናት ከ 6 ሳምንት እስከ 12 ዓመታት ድረስ አገልግሎት ይሰጣል። ነገር ግን የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆች እስከ 19ኛ ዓመት ልደታቸው ድረስ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

የልጆች እንክብካቤ ድጎማ ለሚቀበሉ ልጆች እንክብካቤ መስጠት ይፈልጋሉ?

1. የልጅ እንክብካቤ ድጎማ አቅራቢ ስለመሆን መረጃ ለማግኘት የቅድመ ትምህርት መምሪያን ያነጋግሩ። ለዚህ ፕሮግራም ለማመልከት የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የልጆች እድገት አገልግሎት ሰጪ ሆነው ፍቃድ ያለዎት መሆን አለብዎት። [ፈቃድ ያለው የልጆች እንክብካቤ አቅራቢ ]ስለመሆን መረጃ ያግኙ።
2. ፍቃድ ያለዎት የልጆች እድገት አገልግሎት ሰጪ ከሆኑ እና የልጆች እንክብካቤ ድጎማ ሰጭ መሆን ከፈለጉ፣ በቅድሚያ የግንዘቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም መከታተል ይኖርብዎታል። የምዝገባ መረጃ እና የድጎማ ፕሮግራም የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ-ግብር [እዚህ] ይገኛሉ።
3. በልጆች እንክብካቤ ድጎማ ፕሮግራም ውስጥ እንዲሳተፉ የተፈቀደላቸው አቅራቢዎች ከተፈቀደላቸው አገልግሎት የመስጠት አቅማቸው እስከ 95 በመቶ ድረስ የድጋፍ ቫውቸር የሚቀበሉ ቤተሰቦችን እንዲያገለግሉ ይፈቀድላቸዋል። ስምምነቱ በቅድመ ልጅነት ትምህርት መምሪያ በጽሁፍ ፍቃድ እስኪያገኝ ድረስ ለተሰጠ የልጆች እንክብካቤ አገልግሎት ክፍያ ተመላሽ ሊደረግልዎት አይችልም።

## ማይ ስኩል ዲሲ (My School DC)፥ በዲሲ ውስጥ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች አማራጮችን ይፈልጉ

ማይ ስኩል ዲሲ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ላሉ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የጋራ የሆነ የትምህርት ቤት ማመልከቻ እና የሎተሪ እጣ ድህረ-ገጽ ነው። ስለ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች እና ቻርተር ትምህርት ቤቶች በዲሲ ውስጥ ለማወቅ፣ ለትምህርት ቤቶች ለማመልከት፣ እና ልጅዎትን በዲሲ ትምህርት ቤት ውስጥ ለማስመዝገብ የማይ ስኩል ዲሲ ድህረ-ገጽን ይጎብኙ፥ http://www.myschooldc.org/

## በትምህርት ቤት ለመመዝገብ የዲሲ ነዋሪ መሆንዎትን ያረጋግጡ

በማንኛውም የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ ለመመዝገብ፣ ወላጅ ወይም የመጀመሪያ እንክብካቤ ሰጭ በዲስትሪክቱ ውስጥ በባህላዊ የህዝብ ወይም ህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ለተመደበ ወይም መማር ለሚፈልግ ለእያንዳንዱ ተማሪ የዲሲ ነዋሪነትን ማረጋገጫ ዋና ሰነዶችን ማቅረብ አለባቸው። ነዋሪነትን ለመወሰን በትክክል የተጠናቀቀ [የዲሲ የነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጽ ]መሞላት አለበት።
ከሚከተሉት አንዱ የዲሲ ነዋሪነትን ለመመስረት ተቀባይነት አለው፥

- የደሞዝ ክፍያ ማስረጃ፣
- ተጨማሪ የደህንነት ገቢ ዓመታዊ የጥቅማጥቅ ማሳወቂያ፣
- በዲሲ የግብር እና የገቢ ጽ/ቤት የተረጋገጠ የ D40 ቅጽ ቅጂ፣
- የወታደር የመኖሪያ ቤት ትእዛዝ፣
- የኤምባሲ ደብዳቤ፣
- ልጁ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ክልል ውስጥ እንደሆነ የሚያሳይ ማስረጃ፣ በፍርድ ቤት ትእዛዝ መልክ፣ እና
- ከዲሲ መንግሥት የገንዘብ እርዳታ መኖሩን ማረጋገጫ፣ ከሚከተሉት በአንዱ መልክ፥
- ለችግረኛ ቤተሰቦች ጊዜያዊ እርዳታ (TANF - ቲ.ኤ.ኤን.ኤፍ) የገቢ ማረጋገጫ ማሳወቂያ ወይም በድጋሚ ብቁ ለመሆን የማረጋገጫ/የማጽደቂያ ደብዳቤ፣
- የሜዲክኤይድ የማጽደቂያ ደብዳቤ ወይም በድጋሚ ብቁ ለመሆን የማጽደቂያ ደብዳቤ፣
- የተጠሪውን ስም እና ስልክ ቁጥር የያዘ ከመጠለያ ቤቶች የተሰጠ የመኖሪያ ቤት የድጋፍ ደብዳቤ፣ ወይም ከመኖሪያ ቤቶች ባለስልጣን የተሰጠ ደብዳቤ፣ ወይም

- ከሌላ የዲሲ መንግሥት ፕሮግራም የሚገኝ የገንዘብ ድጋፍ መኖሩን ማረጋገጫ።
- የዲሲ ነዋሪነትን ለማረጋገጥ ከላይ የተገለጹት አንዳቸውም ሰነዶች መቅረብ ካልቻሉ፣ ከሚከተሉት ሁለቱ ያስፈልጋሉ፥
- ጊዜው ያላለፈበት የዲሲ የሞተር ተሽከርካሪ ምዝገባ፣
- ጊዜው ያላለፈበት የሊዝ ውል ወይም የኪራይ ስምምነት፣
- ጊዜው ያላለፈበት የዲሲ የሞተር ተሽከርካሪ የስራ ፈቃድ ወይም ሌላ የመንጃ ፍቃድ ያልሆነ ህጋዊ መታወቂያ፣ እና
- የቤት ውስጥ የፍጆታ ክፍያ ደረሰኝ (የጋዝ፣ የመብራት እና የውሃ ደረሰኞች ብቻ ተቀባይነት ያላቸው)።

ነዋሪነትን ለመወሰን ኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ ተጨማሪ ሰነዶችን ሊጠይቅ ይችላል። የነዋሪነት ሁኔታን ለማረጋገጥ ቤተሰቦች ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ሰነዶች እንዲያቀርቡ ሊጠየቁ ይችላሉ፥

- የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫ ቅጾች
- ሌሎች የመጀመሪያ እንክብካቤ ሰጭ ቅጾች
- የቤት ጉብኝት ቅጾች
- ርዕስ X ክፍል C የማክኪኔይ-ቬንቶ የምስጢራዊነት ሪፈራል ቅጽ

## የዲሲ ነጻ የበጋ ምግብ ፕሮግራም

የዲሲ ነጻ የበጋ የምግብ ፕሮግራም ትምህርት ቤት በሚዘጋበት ወቅት በሰኔ፣ በሐምሌ እና ነሐሴ ወራት ለልጆች ነጻ፣ የተመጣጠነ ምግብ እና ቀለል ያሉ ምግቦችን (ስናክ) ለመመገብ የተነደፈ የፌዴራል የምግብ ፕሮግራም ነው። የምግብ አገልግሎት ለማግኘት ምንም ማመልከቻ የማያስፈልግ ሲሆን ፕሮግራሙ እድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በታች ለሆኑ ልጆች ሁሉ ነጻ ነው። አገልግሎቱን ለማግኘት ልጆች በምግብ ሰዓት የዲሲ ነጻ የበጋ ምግብ ጣቢያን መጎብኘት ብቻ ይጠበቅባቸዋል። ዲሲ ነጻ የበጋ ምግብ ጣቢያዎች የዩ.ኤስ.ዲ.ኤ (USDA) መመሪያዎችን የሚያሟሉ የተመጣነ ይዘት ያላቸውን ምግቦች ያቀርባሉ። ብዙ የመመገቢያ ጣቢያዎች በተጨማሪም ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አዝናኝ እና ጠቃሚ እንቅስቃሴዎችን ያቀርባሉ። ለእርስዎ ቅርብ የሆነ የዲሲ ነጻ የበጋ ምግብ ጣቢያን ከዚህ ድህረ-ገጽ ያግኙ፥

https://www.fns.usda.gov/summerfoodrocks

## የግጭት መፍትሄ ሰጭ ጽ/ቤት፥ የፍትህ ሂደት ችሎት ጥያቄ

የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ (IDEA - አይ.ዲ.ኢ.ኤ) የአካል ጉዳተኞች ልጆች ወላጆች እና የሕዝብ የትምህርት ኤጀንሲዎች የአካል ጉዳት ያለባቸውን ልጆች ለይቶ በማወቅ፣ በመገምገም፣ የትምህርት ምደባ በመስጠት ወይም ነጻ የሆነ ተስማሚ የሕዝብ ትምህርት ለልጁ በማቅረብ ዙሪያ የተፈጠሩ አለመስማማቶችን ለመፍታት የሚያስችል አድሏዊ ያልሆነ የይግባኝ ፍትህ የችሎት ጥያቄ ለማንሳት እድሉ ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የአሰራር ሂደት እያንዳንዱ እስቴት እና የኮሎምቢያ ዲስትሪክት እንዲመሰርቱ እና እንዲጠቀሙ ይጠይቃል። በእስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት (OSSE- ኦ.ኤስ.ኤስ.ኢ) ስር የሚገኘው የግጭት መፍትሄ ሰጭ ጽ/ቤት የልዩ ትምህርት የፍትህ ችሎት ሂደት የማካሄድ ኃላፊነት አለበት።

የልዩ ትምህርት የይግባኝ ችሎት ሂደት ለወላጆች እና ለሕዝብ የትምህርት ኤጀንሲው አለመግባባቱ ባስከተለው ጉዳይ (ጉዳዮቹ) ዙሪያ ያላቸውን አመለካከት እና ሃሳብ ስልጠና ለወሰደ፣ ገለልተኛ ለሆነ እና ለማያዳላ የሰሚ ችሎት መኮንን በምስክሮች እና ሰነዶች በተጨባጭ ለማሳየት እድሉን ይሰጣቸዋል። የይግባኝ ችሎቱ ባለስልጣናት የዲስትሪክቱ የህዝብ ትምህርት ሥርዓት ቅጥር ሰራተኞች አይደሉም። ችሎቱ ከተካሄደ በኋላ፣ የይግባኝ ሰሚ ባለስልጣኑ አለመግባባት ባስከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፤ ይህንንም ለወላጅ እና ለሕዝብ የትምህርት ኤጀንሲው ያሳውቃል። የፍትህ ሂደት ችሎት ውሳኔ በፍርድ ቤት ይግባኝ ሊባል ይችላል።

አይ.ዲ.ኢ.ኤ የፍትህ ሂደት ችሎት በሚጠይቁበት ጊዜ ሁለቱም ወገኖች የተወሰኑ አካሂዶችንን እንዲከተሉ የሚያስገድድ ሲሆን ወላጅ፣ የሕዝብ የትምህርት ኤጀንሲው፣ እና የችሎት አቤቱታ ሰሚ መኮንኑ ሊከተሏቸው የሚገቡ የተወሰኑ የጊዜ ገደቦች እና ደንቦች አሉ። ይህ አሰራር በሚከተላቸው የአሰራር ሂደቶች እና የፍርድ ሂደቱ ሕጋዊ ባህሪ መኖር ምክንያት፣ አብዛኛውን ጊዜ ወላጆች የሚወክላቸው ጠበቃ ይኖራቸዋል፣ ነገር ግን ራሳቸውን መወከልም ይችላሉ።

የፍትህ ሂደት የቅሬታ ማቅረቢያ ቅጾች በእንግሊዝኛ እና በአማርኛ ቋንቋዎች ይገኛሉ። ለቤተሰቦች እና ለተማሪዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ የግጭት መፍትሄ ሰጭ ጽ/ቤት ድህረ ገጽን ይጎብኙ፥ https://osse.dc.gov/service/office-dispute-resolution-resources-parents-and-students

## የቋንቋ ተደራሽነት አገልግሎቶች፥

ለንግግር ቋንቋ አስተርጓሚ እና/ወይም ለትርጉም፣ እባክዎትን የኤጀንሲውን የቋንቋ ተደራሽነት አስተባባሪን ያነጋግሩ፥

ኤልሳ ተክለሃይማኖት - በኢሜይል፥ elsa.teklehymanot3@dc.gov ወይም በስልክ፥ (202) 727-6436

አድራሻ፥

Office of the State Superintendent of Education

1050 First St. NE

Washington, DC 20002

ስልክ፥ (202) 727-6436